# ግልጽነት፣ መልካም አስተዳደር፣ እና ከሙስና ነጻ ስለመሆን

ግልጽነት የመልካም አስተዳደር መሰረትና ሙስናን ለመዋጋትም የመጀመሪያው ቀዳሚ እርምጃ ነው።  እንዲሁም ግልጽነት  በየትኛውም ቦታ ቢሆን መልካም የመዝገብ እና የማህደር አያያዝ አመራር ሥርዓት፣ እና የገንዘብ አያያዝ አመራርና ቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር እንደዋና አመክንዮ ሆኖ ያገለግላል። እንዲሁም ማህበራዊ ሃላፊነት ከሚሰማው ደራሲነት ወይም ጋዜጠኛነት፣ ከአርትዖት ሥራ፣ ከአታሚነት እና በማናቸውም ዓይነት የሚዲያ መጠቀሚያ ዘዴ መረጃን ከማሰራጨት ሥራ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው።

ሙስና መሰረታዊ ማህበራዊ ዕሴቶችን በእጅጉ ይጎዳል፤ የህግ የበላይነትን አደጋ ላይ ይጥላል፤  የፖለቲካዊ ተቋማትን ተአማኒነት ይሸረሽራል፤ በንግድ ማህበረሰቡ ውስጥ ሙሰኞች ብቻ የሚበለጽጉበትን ሁኔታ ይፈጥራል። የሳይንስ ስራና ምርምርን ያደናቅፋል፤ የባለሙያዎችን የዕለት ተዕለት ተግባር ያዳክማል፤ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ማህበረሰብ እንዳይገነባ እንቅፋት ይፈጥራል። ሙስና ለሰው ልጆች ሰቆቃና ስቃይ ምክንያትና ይሄው ሁኔታም ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ዋነኛውን አስተዋጽዖ የሚያደርግ ሲሆን የማህበራዊ ዕድገትም ጠንቅ ነው። ሙስና ሁልጊዜም ምስጢራዊነትና አላዋቂነት በነገሰባቸው ስርአቶች ውስጥ የበላይነትን ይይዛል።

ቤተመፃህፍት ትክክለኛና ሚዛናዊነት ያልጎደላቸውን የትምህርት፣ የሳይንስ፣ የቴክኒክና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን መረጃዎች ለእያንዳንዱና ለሁሉም ለማቅረብ በቁርጠኝነት የቆሙ በተፈጥሯቸው ግልጽነት ያላቸው ተቋማት ናቸው ብሎ አለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን አበክሮ ይገልጻል። በቤተመፃህፍትና በመረጃ አገልግሎት ተቋማት የሚቀርቡ የመረጃ አቅርቦቶች የዜጎችን እውቀት በማዳበርና ውይይቶችንና ክርክሮችን በማበልፀግ መልካም አስተዳደር እንዲኖር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

ቤተ-መፃህፍትና የመረጃ አገልግሎት ተቋማት መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተልዕኳቸውን ማስፋት ይገባቸዋል። በተለይም ዜጎች መብቶቻቸውን በሚገባ እንዲያውቁ በመርዳት በኩል እጅግ ከፍ ያለ ሚና መጫወት ይችላሉ።

**ስለዚህ የቤተ-መፃህፍትና የኢንፎርሜሽን ሥራ ባለሙያዎች እና በብሄራዊና በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ ቤተ-መፃህፍትንና የኢንፎርሜሽን አገልግሎቶችን የሚያስተዳድሩ ሁሉ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ፕሮግራሞች እንዲደግፉ አለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ጥሪ ያቀርባል።**

1. ቤተመፃህፍት የቤተ-መፃህፍት አገልግሎት ሙያን በቀጥታ ሊጎዱ ከሚችሉ ለምሳሌ ከቤተመጻህፍት መገልገያዎች አቅርቦትና ግዢዎች፣ ከቤተመፃህፍት ባለሙያዎች አሿሿም፣ እና እንዲሁም የቤተመጻህፍት ውሎችን ከማስፈጸምና ከሂሳብና ገንዘብ አስተዳደር ጋር የተገናኙ የሙስና አዝማሚያዎችን መዋጋት ይኖርባቸዋል። የቤተ-መፃህፍት ማህበራትም የሙያ ስነምግባር ደንብ በማውጣት ወይም ያለውን በማጠናከር ቤተመፃህፍቱ ከዚህ አንጻር የሚያደርጉትን ጥረት ሊደግፉላቸው ይገባል።

2. የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች የሁሉንም የኢንፎርሜሽን ሙያተኞች የሙያ ክብር ከፍ ለማድረግ በመጣርና ባለሙያዎቹ የተሻለ ክፍያ እንዲያገኙ በማገዝ ለሙስና የመጋለጥ አዝማሚያዎችን ለመቀነስ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

3. የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች ጠቃሚ ስብስቦችን በመያዝና እንዲሁም የፍልስፍና፣ እና ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አቅርቦት በማመቻቸት ህብረተሰቡን የማስተማር ሚናቸውን እንደገና ማረጋገጥ ይገባቸዋል።

4. የሚገኙበት ሀገር የመረጃ አቅርቦት የተመቻቸበት ወይም መረጃን የማግኘት ነጻነት ህግ ያለበት ሀገር ከሆነ የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች ቤተመፃህፍቱን ዜጎች መረጃ የሚለዋወጡባቸው ማእከላት እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

5. የሚገኙበት ሀገር የመረጃ አቅርቦት ያልተመቻቸበት ወይም መረጃን የማግኘት ነጻነት ህግ የሌለበት ሀገር ከሆነ ወይም ያሉት ህጎች ውጤታማ ካልሆኑ የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች እነዚህ ህጎች የሚረቀቁበትን፣ ወይም የሚሻሻሉበትን እና ህብረተሰቡ እንዲያውቃቸው የሚደረግበትንና እንዲሁም ህጎቹ እንዳይዘነጉ የሚደረጉ ጥረቶችን ሊደግፉ ይገባል።

6. ዜጎች ህጎቹን በቅጡ ለመረዳት ያላቸውን አቅም ለማዳበርና መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉትን ጥረት የሚደግፉ መረጃዎች የትኞቹ እንደሆኑ በአግባቡ ለመለየት እንዲችሉ ለቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎችና ለቤተ-መፃህፍት ተጠቃሚዎች ስልጠና ሊመቻችላቸው ይገባል።

7. ቤተ-መፃህፍት በህግ እውቅና ካላቸው ክፍሎች የሚገኙ መረጃዎችን በተለይም የዜጎችን መብቶች የሚመለከቱ የመረጃ ስብስቦችን መያዝ ይጠበቅባቸዋል። ከእነዚህ በህግ እውቅና ካላቸው ክፍሎች የሚገኙ መረጃዎች ሁሉም በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችል እንዲሆኑና እንዲሁም ቀላል ማውጫዎችንና የጽሁፎችን አጭር መግለጫዎች በማዘጋጀትና የመረጃ ፍለጋ ድጋፍ በመስጠት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባቸዋል። በተጨማሪም ህጎችንና የሰው ልጆችን መብቶች የሚመለከቱ ይፋዊ መረጃዎች በዘመናዊ የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝ ዘዴ (digitization)እንዲያዙ እና እንዲጠበቁ ፕሮግራሞችን ማደራጀት የሚጠበቅባቸው ሲሆን እንዲሁም እነዚህን መሰል መረጃዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርጉ ተገቢ ነው።

8. ቤተ-መፃህፍት ፖስተሮችንና ሌሎች የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም ራሳቸውን መረጃን የማግኘት መብት ማስተዋወቂያ ማእከል አድርገው መደራጀት የሚኖርባቸው ሲሆን የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች ደግሞ ህብረተሰቡ መረጃን ስለማግኘት መብት ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲል ተገቢውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

9. ቤተ-መፃህፍት ከመንግስታዊ የመረጃ ምንጮች፣ በጸረሙስና እንቅስቃሴ ላይ ከተሰማሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ክፍሎች የሚገኙ መረጃዎችን የሚይዙባቸው የመረጃ ቋት ማእከላትን ማደራጀት ወይም እነዚሁ እንዲደራጁ ከሚሰሩ አካላት ጋር በመተባበር መስራት ይኖርባቸዋል።

10. ቤተ-መፃህፍት በጸረሙስና እንቅስቃሴ ላይ የተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላቋቋሚቸው ወይም ሊያቋቁሚቸው ላቀዷቸው የዜጎች የምክር ማዕከላት መረጃዎችን በማቅረብ፣ የዳታቤዛቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠትና እንዲሁም በማናቸውም የሙያ ብቃታቸው በመደገፍ ከጎናቸው ሊቆሙ ይገባል።

**በአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ከፍተኛ አመራር አካል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 3 ቀን 2008 የጸደቀ**